ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)
8 ኛ ሳምንት
አብርሃም ሳራና የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን

የትምህርቱ ዓላማ

- ስለአብርሃም፣ እግዚአብሔር ስለገባለት ቃል ኪዳንና እግዚአብሔር ቃሉን እንደፈፀመለት መማር ነው፡፡

ምንባብ

- ዘፍጥ.18 እና 21

መግቢያ

- ዛሬ አብርሃም ስለተባለው ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው እንማራለን፣ አብርሃም ዓለም በጥፋት ውሃ ከጠፋች በኋላ የተነሳ ነው፡፡ የጥፋት ውሃን ታስታውሳለችሁ? ለመምህር አስረዱ

ትምህርቱ

- የጥፋት ውሃ ከተከሠተ ከረጅም ዓመታት በኋላ፣ አብርሃም የተባለ ፃድቅ ሰው ነበር፡፡
- ኖህ ከጥፋት ውሃ እንዴት እንዳዳነ ታስታውሳላች?
- አብርሃም ሳራ የተባለች ሚስት ነበረችው፡፡ ድሆችን የሚረዱና ብዙ ሀብትም የነበራቸው ሲሆን ልጆች ግን አልነበሯቸውምና እግዚአብሔር ልጅ እንደሚሠጣቸው ቃል ገባላቸው፡፡ ለብዙ ዓመታት ቢጠብቁም ልጅ ሳያገኙ አረጁ፡፡
- አንድ ቀን እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገልጦ «ልጅ አሠጥሃለሁ ሚስትህ ሳራም ልጅ ትወልዳለች» አለው፡፡እግዚአብሔር እንደተናገረው አብርሃምና ሳራን አሰባቸው ልጅም ሠጣቸው የተወለደውንም ይስሀቅ አሉት፡፡
- አብርሃም 100፣ ሳራ 90 ዓመት ሲሆናቸው ይስሀቅን አገኙ፡፡ ብዙ የልጅ ልጆችም እንደሚሠጠው ቃል ገባለት፡፡

ጥያቄ

1.እግዚአብሔር ለአብርሃም እና ለሳራ ቃል የገባላቸው ምን ነበር?

ሀ. ልጅ ለ. ትልቅ ቤት

2.እግዚአብሔር ቃሉን ፈጸመላቸው?

ሀ. አዎ ለ. አይደለም

3. የቃል ኪዳኑ ልጅ ስም ማን ነበር?

ሀ. አብርሃም ለ. ይስሐቅ ሐ. አዳም

ተግባር፣

1.ሥዕሉን በቀለም ቀቡ፡፡ ሌላ ሥዕልም ሳሉ፡፡

2. የሚከተለውን መዝሙር ዘምሩ

መዝሙር

ለጌታዬ ለእግዚአብሔር ስላደረገልኝ ምን እከፍለዋለሁ፣

ምስጋና ነው እንጂ (2) ሌላ ምን እላለሁ(4)፣

ይቆየን፡፡